# ግራ የገባቸው



ዳሩ አልቆ ካቻምና ፤ መሃሉ ዳር ሆኖ
ለባዕድ ተችሮ ፤ ምድር ተሸንሽኖ
እህሉ ከቀዬው ፤ ተመርቶ ተጭኖ
አገሬው ሲበላ ፤ የራሱን ለምኖ
ታጋይ ነኝ የሚለው ፤ አይኖቹን ጨፍኖ
ግራ ግራ ይላል ፤ ከቅዠቱ ባኖ
መታገል ሲሳነው ፤ በፍርሃት ታፍኖ ።

ዶ/ር ኢንጂነሩ ፤ ተማሩ ያልናቸው
ትግል የግል ጥቅም ፤ መገንቢያ መሰሏቸው
የተፈጥሮ ፀባይ ፤ ጠልፎ ሲጥላቸው
ግራ ግራ ይላሉ ፤ ግራ የገባቸው ።

እኔን ግራ ይግባኝ ፤ እነ ግርግሩ
ወሬ እያጣፈጡ ፤ ሥራ እንኳ አይሰሩ
ሀሞተ ቆፍጣና ፤ ሰው ጠፍቶ ባገሩ
ትግል አደረጉት ፤ ታጋይ ማማረሩ ።

ታዛቢው

November 30/2009